# ቃየን ሚስቱን ከየት አገኘ[1]?

**ጥያቄ:** ዘፍጥረት 4:1 ላይ አዳምና ሔዋን ቃየንን እንደወለዱ እርሱም የበኩር ልጃቸው እንደሆነ ተጽፏል። አስከትለውም ታናሽ ወንድሙን አቤልን ወለዱ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ቃየን ወንድሙን አቤልን ገደለው (4:8)። ከዚያ በኋላ ቃየን ሚስቱን እንዳወቃትና እንደጸነሰች ሄኖህንም እንደወለደች ይመሰክራል (4:16)። ለመሆኑ ቃየን ያገኛት ሚስቱ ከየት መጣች? ከአዳም ሌላ የተፈጠሩ ሌሎች ሰዎች ነበሩ እንዴ?

**መልስ:** ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በመጀመሪያ መረዳት ያለብን በአንድ ዐረፍተ ነገርና በሚቀጥለው መካከል ያለውን የጊዜ ልዩነት ነው። አንድ ድርጊት ሲፈጸም የሚፈጀው ጊዜና ታሪኩ ሲተረክ የሚወስደው ጊዜ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ ያህል የመኪና አደጋ ሲደርስ አደጋው የሚፈጀው ጊዜ በሰከንዶች ቢቆጠር ነው (ቢበዛ በደቂቃ)። ነገር ግን አደጋውን በቃል ለመተረክም ሆነ በጽሑፍ ለማስፈር የሚፈጀው የጊዜ እርዝመት አደጋው ከደረሰበት ጊዜ እንደሚበልጥ ግልጽ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ  የድርጊቱ ጊዜ ከትረካው ጊዜ ሊበልጥ ይችላል። ለምሳሌ ያህል ብንወስድ ሉቃስ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የምድር ላይ የልጅነት ዘመኑን በአጭሩ እንዲህ ሲል ገልጾታል-"**ሕጻኑም አደገ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ (ሉቃስ 2:40)።**" ማርቆስ 1:32-34 ላይ ጌታ ኢየሱስ በሽተኞችን እንደፈወሰ ይናገርና ቁጥር 35 ላይ ደግሞ ማለዳ ተነስቶ ሊጸልይ ወደምድረ በዳ እንደሄደ ይተርካል። በሁለቱ ቁጥሮች መካከል ብዙ ሰዓታት አልፈዋል። አንባቢዎቹም ይሄ ይገባቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ማብራሪያ ሲጨመርበት ድርጊቱ ከተፈጸመበት ጊዜ በላይ የሚፈጅ ሐተታ ሊጻፍ ይችላል።

ወደ ጥያቄያችን እንመለስና የቃየንን ጉዳይ በዚህ መረዳት ውስጥ ሆነን በድጋሚ እንመልከት። በምዕራፍ 4:15 ና በቁጥር 16 መካከል ምን ያህል ዘመናት እንዳለፉ አልተነገረንም። አንድ ሴት ባል አገባች ብለን ጽፈን ቀጥለን ደግሞ ከእርሱም ልጅ ወለደች ብንል ሥርዓቱን ጠብቀው እስከተጋቡ ድረስ በተጋቡ ዕለት ወይም ደግሞ በሳምንቱ እንዳልወለደች እንረዳለን። ምክንያቱም ልጅ ተገቢውን የጊዜ ሕግጋት ጠብቆ እስከተወለደ ድረስ ቢያንስ ቢያንስ በአገባችበትና በወለደችበት መካከል ከሰባት እስከ ዘጠኝ ወር እንደሚኖር ጥርጥር የለውም (በጤንነት ጉድለትና ሌሎች ምክንያቶች

---

[1] ይህንን ጽሑፍ ለንግድ ሥራ አባዝቶ መጠቀም በሕግ የተከለከለ ነው። መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። መሓሪ የትምህርት አገልግሎት መጋቢት 2000 ዓመተ ምህረት።

በሐኪሞች እርዳታ ቀድማ እስካልወለደች ድረስ)፡፡ ስለዚህ “*ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ ከዔድንም ወደ ምሥራቅ በኖድ ምድር ተቀመጠ* (4፡16)” በሚለውና “*ቃየንም ሚስቱን አወቀ ፀነሰችም ሄኖህንም ወለደች* (4፡17)፡፡” በሚለው ቁጥር መካከል የጊዜ ክፍተት መኖሩ አያጠራጥርም፡፡

ቃየን ሚስቱ ማን እንደሆነች ለማወቅ ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1-4 ድረስ የተፈጸመውን ነገር ግን አጥሮ እንደ አርዕስተ ዜና የተጻፈውን ምዕራፍ አምስትን እንይ፡፡ ዘፍጥረት 5፡4-5 ላይ “**አዳምም ሴትን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ ዓመት ሆነ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፡፡ አዳምም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ሆነ ሞተም፡፡**[2]” ብሎ ይናገራል፡፡ አዳም 930 ዓመታት ሲኖር ብዙ ልጆችን እንደወለደ ከተነገረን ቃየን ያገባት ሚስቱ እህቱ አለያም የወንድሙና የእህቱ ልጅ ልትሆን ትችላለች፡፡ ምክንያቱም በዚያ ጊዜ የነበሩት አዳምና ቤተሰቦቹ በመሆናቸው ወንድ ሴት እህቱን እንዳያገባ የሚከለክል ሕግ አልነበረምና፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት “እግዚአብሔር በዔድን ገነት ያንን ዛፍ ለምን ተከለ?” የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ እንድንመልስላችሁ የምትሹት ጥያቄ ቢኖራችሁ በአድራሻችን (mywongel@yahoo.com) ላኩልን እናስተናግዳለን፡፡

---

[2] ይህንን ጽሑፍ ለንግድ ሥራ አባዝቶ መጠቀም በሕግ የተከለከለ ነው፡፡ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ መሓሪ የትምህርት አገልግሎት መጋቢት 2000 ዓመተ ምህረት፡፡